ለሁለተኛ ጊዜ የወጣ ክፍት የስራ ቦታ ማስታወቂያ

የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ በሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር በወጣው አዲሱ የከፍተኛ ትምህርት አመራሮች ምልመላና ምደባ መመሪያ መሰረት ቀጥሎ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟሉትን እና ዩኒቨርሲቲውን በፕሬዚዳንትነት ለመምራት ፍላጎቱና ብቃቱ ያላቸውን አመልካቾች አወዳድሮ ከፍተኛ ውጤት ያመጣውን/ችውን ተወዳዳሪ የዩኒቨርስቲው ፕሬዚዳንት አድርጎ ለመመደብ ይፈልጋል፡፡

1. ስለተቋሙ አጭር መግለጫ

አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ በኢትዮጵያ እና በአለም አቀፍ ደረጃ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ትምህርትና ምርምር ሥመ-ጥር ከሚባሉ ዩኒቨርሲቲዎች መካከል አንዱ በመሆን በምርምር አመርቂ ስራ እንዲሰራ ታቅዶ የተመሠረተ ዩኒቨርስቲ ነው፡፡ ከ7000 በላይ ተማሪዎችን፣ ከ600 በላይ የሚሆኑ መምህራንና፣ ተመራማሪዎችን እንዲሁም ከ500 በላይ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችን የያዘ ሲሆን ላለፉት ስምንት ዓመታት በርካታ የድህረ-ምረቃና የቅድመ-ምረቃ ፕሮግራሞችን በመክፈት፣ ታላላቅ ሀገራዊ ፋይዳ ያላቸውን የምርምር ስራዎችን በማከናወንና ከፍተኛ ጠቀሜታ ያላቸውን ማህበራዊ አገልግሎቶችን በመስጠት ላይ የሚገኝ ከፍተኛ የትምህርትና የምርምር ተቋም ነው፡፡

2. የስራው መደብ

የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት

3. የማመልከቻ መስፈርቶች

3.1. **የትምህርት ደረጃ፡-** በሳይንስ ኢንጂነሪንግና ቴክኖሎጂ መስኮች ሶስተኛ ድግሪ (PhD) ወይም ሁለተኛ ድግሪ (MSc) እና ቢያንስ የረዳት ፕሮፌሰርነት ማእረግ ያለው/ያላት፤

3.2. **የሥራ ልምድ፡-** በከፍተኛ ትምህርት፣ በኢንዱስትሪ፣ በሣይንስና ቴክኖሎጂ ምርምር ተቋማት ወይም መሰል ተልዕኮ ባላቸው ተቋማት አመራር/ኃላፊነት እርከን ያገለገለ/ች፤ በተጨማሪም በአለም አቀፍ የሣይንስና ቴክኖሎጂ የምርምር ተቋማት በአመራር ላይ የቆየ/ች ቢሆን ይመረጣል፡፡

3.3. **ስትራቴጂያዊ እቅድ ማቅረብ፡-** አመልካቾች በዩኒቨርሲቲው የከፍተኛ ትምህርትን ተደራሽነት፣ ፍትሃዊነት፣ ጥራት፣ ተገቢነትና ዓለምአቀፋዊነት ለማሳካት ስለሚከተሉት ስልት፤ ዩኒቨርሲቲውን በሳይንስና ቴክኖሎጂ የልህቀት ማዕከል ለማድረግ ስለሚሰጡት አመራር ከ10 ገጽ ያልበለጠ ስትራቴጂያዊ እቅድ በፅሁፍ ያቀርባሉ፤ ስላቀረቡት እቅድ ለዩኒቨርሲቲው አካዳሚክ ስታፍና ሰራተኞች እንዲሁም ተማሪዎች በሚዘጋጀው መድረክ ላይ ገለፃ ያደርጋሉ፤

3.4. **ፆታ፡-** ማስታወቂያው ወንዶችንና ሴቶችን የሚያጠቃልል ሲሆን፣ መስፈርቱን የሚያሟሉ ሴቶች እንዲያመለክቱ ይበረታታሉ፤

4. **ተፈላጊ ክህሎቶች**

4.1. **የአመራር ክህሎት፡-** አመልካቾች በዩኒቨርሲቲው ያለውን የሰው፣ የገንዘብና የቁሳቁስ ሃብት በማስተባበር፣ ለመምራት የሚያስችል ዕቅድ በማቀድ፣ የአሠራር፣ የክትትል፣ የድጋፍና ቁጥጥር ሥርዓትን በመዘርጋት፣ ኃላፊነትንና ተጠያቂነትን በማስፈን የአካዳሚክ፣ ምርምርና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞችን የሥራ ተነሳሽነትና የባለቤትነት ስሜት ለማሳደግና ዩኒቨርሲቲውን በሣይንስና ቴክኖሎጂ ያለውን ተልዕኮና ራዕይ ለማሳካት የሚያስችል የአመራር ክህሎት ያላቸው መሆን አለባቸው፤

4.2. **አዲስ አሰራር የመፍጠርና ለውጥ የማምጣት ክህሎት፡-** አመልካቾች በዩኒቨርሲቲው ለውጥና እድገትን ለማምጣት የሚያስችሉ በሣይንስና ቴክኖሎጂ ዘርፍ አዳዲስ የአሰራር ስልቶችን የማመንጨትና ተግባራዊ የማድረግ አቅም ያላቸው መሆን አለባቸው፤

4.3. **የተግባቦት ክህሎት፡-** አመልካቾች በዩኒቨርሲቲውም ሆነ ከዩኒቨርሲቲው ውጭ ካሉ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ አገራዊ፣ አህጉራዊና አለምአቀፋዊ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት በመፍጠር የዩኒቨርሲቲውን በሣይንስና ቴክኖሎጂ ያለውን ተልዕኮና ራዕይ ለማሳካት የሚያስችል የተግባቦት ክህሎት ያላቸው መሆን አለባቸው፣

5. ተፈላጊ ሥነ-ምግባር

5.1. አመልካቾች ከሥነ-ምግባር ጉድለቶች የፀዱ፣ በመልካም ባህርያቸው፣ በስራ አክባሪነታቸውና ታታሪነታቸው እንዲሁም፣ ለሌሎች አርአያነታቸው የጎላ መሆኑ የተመሰከረላቸው፤

5.2. አመልካቾች ተግባብቶ የመስራት፣ ሁሉን በእኩል የማስተናገድ፣ ለሚቀርቡላቸው ጉዳዮች ተገቢውን ምላሽ በተገቢው ጊዜ የመስጠት መርህ የሚከተሉ መሆን አለባቸው፣

6. የምደባ ሁኔታ

በውድድሩ የተመረጠው/ችው አመልካች የአዲስ አበባ ሣይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንት ሆነው የሚመደቡ ሲሆን የአመራር ብቃታቸው በየጊዜው እየተገመገመ ለስድስት አመታት የሚያገለግሉ ይሆናል፡፡ እንደአስፈላጊነቱ የአገልግሎት ጊዜው ሊራዘም ይችላል፤

7. ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም

በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ስኬል መሰረት፤

8. የማመልከቻ ጊዜ

አመልካቾች ማመልከቻቸውን፣ CV እና የትምህርት እና የሥራ ልምድ ማስረጃቸውን ኮፒ እንዲሁም ከ10 ገጽ ያልበለጠ ስትራቴጂያዊ እቅድ ማስታወቂያው በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 21 ቀናት ውስጥ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፤

9. የማመልከቻ ቦታ

አዲስ አበባ ሣይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት አስተዳደር ሕንፃ፣ 3ኛ ፎቅ፣ ቢሮ ቁጥር 305፤ የቢሮ ስልክ ቁጥር +251118961443.

10. የማመልከቻ ማቅረቢያ መንገዶች

10.1. በዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት ዳይሬክቶሬት በግንባር ቀርቦ በመመዝገብ፤

10.2. በዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት ዳይሬክቶሬት ኢ-ሜይል አድራሻ presidentsearch2019@aastu.edu.et በመላክ፤

10.3. በፖስታ ሳጥን ቁጥር አድራሻ አዲስ አበባ ሣይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት ፖ.ሳ.ቁ. 16417 አዲስ አበባ በመላክ፤

11.ለተጨማሪ መረጃ በሚከተሉት መንገዶች መጠቀም ይቻላል

11.1 በዩኒቨርሲቲው ህዝብና ዓለም-ዓቀፍ ግንኙነት ዳይሬክቶሬት ጽ/ቤት ስልክ ቁጥር +251 1 18880610

11.2 በዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት ሞባይል ስልክ ቁጥር +251 9 11995069 ወይም +251911116559

11.3 በአዲስ አበባ ሣይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ድረ-ገፅ www.aastu.edu.et

የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ አመራር ቦርድ